**የኖርወዩ ወያኔ/ታንድ**

ከዮፍታሄ ዘካርያስ

እነሆ! ጽሁፌን ጀመርኩ። ያዳቆነ ሠይጣን ሳያቀስ አይለቅም ነውና ግደይ ዘርአጽዮን “የጓዶቹን ወያኔ ወይም ሞት” መሰል ተመሣሳይ ሙዚቃ ሊደጋግምብን ተነስቷል። ይሄን አቋም ግን በግልጽ አይደለም እያቀረበ ያለው፤ አለቆቹ የሚያቅራሩትን ቅርሻ በማር ለውሶ ተጋቱ ይለል። ሁሌም ብልጦች ነን ባዩች እነ ግደይ። ስለ ወልቃይት/ጠገዴ የማነነት ጉዳይም ግደይ እንደለመደው አንሸዋሮ ሊያቀርብ ጥሯል። አቶ ገብረመድህን አርአያ እድሜና ጤናውን አብዝቶ ይስጣቸውና ስለ ህወሓት/ወያኔና ስለ መሥራቾቹ ማንነት በመረጃ አስደግፈው እስከሁን ሲነግሩን ኖረዋል።

በሚገርም ሁኔታ ግደይ የኖረው ወያኔነቱ አገርሽቶበት ቢቸግረው ራሱን በጥያቄና መልስ አዘጋጅቶ ተጨፈኑ ላሚኝችሁ እያለን ነው። ወይ አለማፈር!። ዛሬ እንኳንስ የእነ ግደይ የጠነዛና እጅ እጅ ያለው ፕሮፓጋንዳቸው ቀርቶ፣ ማርም ሲበዛ ይመራል ይባላል ። ዛሬም ሳያፍር ስለ ትግሬው ነጻ አውጭ ድርጅቱ፣ እሱ በነበረበት ጊዜ የነበረው ህወኃት/ወያኔ “ቅዱስና መሲህ” እንደነበር ሊሰብከን ይዳዳል ፤ ምን አይነት ዓይን አውጣነት ነው..? ዳሩ እነርሱ ምን ገዷቸው!
ወያኔ/ህወሓት አይድንም እንጅ ቢቻላቸው አሁንም ቢሆን በህዝብ ዕልቂት ሂወት ለመዘራት ይፍጨረጨራሉ።
እንደ እባብም ይሳባሉ። እባብ ሰለከላኬ።

የሰሞኑ የግደይ ዘርአጽዮን መርዛማ ትፋት ያቅለሽልሻል። የጭንቅላት ካንሳር አይደንም፤ መጨረሻውም በከባድ ሥቃይ ተሰቃይቶ በሞት መገላገል ብቻ ነው። የትግሬ ነጻ አውጭ ድርጅት መሠራቾች ሁሉም ማለት በሚያስችል ሁኔታ (ከአቶ ገብረመድህን ዓርአያ) በስተቀር በዝቅተኝነት ስሜት የሚሠቃዩ ስለሆኑ እንደ ጭንቅላት ካንሳር ውስጥ ውስጣቸውን እያጥመነመነ ሲያሰቃያቸው የኖረ ተውሳክ አለ፤ የአማራ ጥላቻ ። ህወሓት/ወያኔ ከምደር ተነስቶ በጥላቻ ተውሳክ ራሱን በራሱ መርዞ ሲሰቃይ ቢኖረም፣ የኢትዮጵያን ሃብትና ንብረት ዘርፎ፣ በጉልበቱ በኢትዮጵያ መንበረ - ሥልጣን ሥልጣኑን ተቆጣጥሮ፣ ከእኔ በላይም ሃብታም የለም በሚልበት ዘመን እንኳ፣ ይሄ የዝቅተኝነት ሰሜት በሽታውን ሊደበቅ አልቻለም።

እንዲያውም ጠገበው እየተፉም በድንቁርና እብሪታቸው አሁንም «ህዝብ ይወዳናል» እያሉ ከመደንፋት አልተቆጠቡም። ወገኖቼ! አለመለከፍ ነው። ያልደረሰበት ግልግል ያዋቃል እንዳይሆንብኝ እንጅ የዝቅተኝነት ስሜትን የሚያውቀው ሆኖ የኖረው እንጅ ማንም ሊሆን አይችልም ። ዝቅተኝነት እኮ የሞት ታናሽ ወንድም ነው።

ግደይ ራሱን ጠይቆ ራሱ መልስ የሰጠበት የሚያስመሰለውን የጥያቄና መለስ ተረኩን፣ የዘሬ ነገር ያንዘርዘረኝ ባዩና የትግሬ ነጻ አውጭው ቡድን ደጋፊ ነው ተብሎ በሚታማው ኢትዮ ሚዲያ ላይ ለጥፎ አስነብቦናል። አጀብ ! ተፈጥሮ የበደለውን ተመክሮ አያድነውም። ለእነ ግደይና መሠሎቹ ሁሌም ቢሆን የወያኔ መኖርና አለመኖር የህልውናቸው ጉዳይ ነው።

ይህ የማፍያ ቡድን ሲመሠረት ሞዴሉ አድርጎ የተነሳው “የመሳፍንት አገዛዝ ” ተብሎ በታሪክ የምናውቀውን ዘመነ መሣፍንትን ተላብሶ ስለነበር፣ ለዚህ እጅግ ኋላቀር ለሆነው እሳቤው ደግሞ በአንደኛ ደረጃ አማራን ቀዳሚ ጠላት አድርጎ ፈረጀ መነሳቱ ሃቅ ነው። ይሄንን ሃቅ ድብቁ ህወሓት ዛሬ

ደግሞ ታንድ ግደይ ዘርአጽዮንም አላካደም። ይሁንና አሁን ሊመጻደቅበት የቃጣውና በኢትዮጵያ አገር አጢፊ ሆኖ የወጣውን ድርጅቱን ያኔ ከአጋሮች ጋር ሆኖ ሲመሠረትም ከላይ የጠቀስኩትን እጅግ ኃላቀር የሆነውን አስተሳሳብ በልቡ ይዞ ነበር።

በሌላ በኩል ግደይ ከመስራቾቹ ውስጥ በአንደኛ ደረጃ ጽንፈኛ የሆነ ኮሚኒስታዊ እንደነበርም አብርውት የነበሩት ይናገራሉ። አቶ ገብረመድህን አርዓያ ስለ ወያኔ መስራቾች ወርድና ቁመት ከጅምሮ ጀመሮ እስከአሁኗ ደቂቃ ድረስ ያልመታከት በመረጃና ራሳቸዉም በቅርብ የመረጃ ያከል ናቸውና ስለሚያውቁቸው እየተናገሩም ነው። እነ ገደይና ኣረጋዊ በርሄ የሠሩትን በደልና ግፍ ተናዘው ንስሃ እንደመግባት ከዚህ እና ከዚያ በመረገጥ ማንነታቸውን ሊደብቁ ይፍጨረጨራሉ፡፤

አሁን አሁን ደግሞ እድሜ ለሥልጣኔ የ40 ዓመት ገመናቸው በየ You Tube ቡ ላይ ተዘርግቶ ስለሚገኝ የአደባባይ ምስጢር ሆኗል። ስለዚህ ህወሓት/ወያኔ ማለት የኢትዮጵያ ነቀረሳ ማለት እንደሆነ የኢትዮጵያ ህዝቦች ተረድተዋል።

የበሽታ ከፉ እህል ያስወድዳል እንደሚባለው ከህወሓት/ወያኔ ወጣን ያሉትም ሆኑ አሁንም ሥልጣኑን በአፈሙዝ ጨምድደው ኢትዮጵያን እያተራመሱ የሚገኙት የደደቢት ቅንቅኖች አንድ የሚያደረጋቸው ባህሪ አላቸው። ህዝብን መፈጀትና አገር ማጥፋትን እንደ «ልማት» ቆጠረው የሚጀነኑበትና ባአንፃሩም ህልዉናቸውም የተያያዘ መሆኑ ነው።

ለሰው ልጅ አየር ፣ ውኃ፣ ምግብ እንደሚያስፍልገው ሁሉ ለእነርሱም ወያኔ ህወሓት ሲኖር ሂወት አላቸው፤ ይተነፍሳሉ ። ወያኔ የሚወደቅ ሲመስላቸው ደግሞ ሠማይ ይደፋባቸዋል። ይህ ባህሪያቸው የማይደበቅና ብዙ ጊዜ ሲስተዋል የቆየ ነው። ለምሣሌ ይሄን መሠል አጋጣሚ በ1997 ዓ.ም ህዝባዊ ምርጫ ወቅትም ታይቷል ። ያኔም ቢሆን እነኝሁ ተመሳሳይ ሰዎች ሁሉም ከጎሬቸው ብቅ ብቅ ብለው “በትገሬ ላይ ኢንተርሃሙዌ ታወጀ” እያሉ ያንኑ የራሳቸውን ፈጠራ ሊያሳምኑ ሞከረው ነበር። ጅራፍ እራሱ ገረፎ ራሱ ይጮሃል እንዲሉ። ምክንያት አላቸው። አንድ የሚያስፈራቸው ትልቅ እዉነት አለ። ቢሸሹት የሚከተላቸው፤ ቢደብቁት ፊት ለፊት እየተደቀነ የሚሞግታቸው።

በኢትዮጵያ ከኦሮሞና ከሚጠሉት አማራ አንፃር ቁመናቸውን ሲያዩት እነኝህ ኃይሎች ውህዳን ናቸው። ይሄ ሊደበቅ የማይችል የሚታይ ሃቅ ነው። በዚያ ላይ ደግሞ ራሳቸው በውስጣቸውና ብምናባቸው የፈጠሩት ከደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ አይነት ዝቅተኝነት ሰሜት አለ። ይህ በሽታቸውን እያወቁትም ቢሆን ያንደፋድፋቸዋል እንጅ ለተመልካች ግን አይደበቅም። እኛም ብንሆን ይሄንን ስሜታቸውን የተረዳነው ቆይተን በተግባራቸው እና በሚያንፀባርቁት በደንቆሮ እብሪታቸው ነው። ሌላ ምንም ዓይነት ፍልስፍና አያስፈልገዉም። በሽታ፣ በሽታ ነው፤ አያድረስ ከማለት ሌላ ምን ይባላል ?

ዛሬ ደግሞ እነዚህ ሁለቱ ትላልቅ ብሄሮች አንድ ላይ እጅ ለእጅ ተያይዘው ይሄንን አገራ አፈረሽ ቡድን ከፉኛ ተገዳድረውታል። እናም የትግሬው ነጻ አዉጭ ድርጅት ተጨንቋል። የህዝቡ ቁጣ ብርክ አስይዟቸዋል። ይህ ብቻ አይደለም። የእነ ግደዩ የትግሬ ነጻ አውጭ ተቋም ህወሓት፣ ጨምድደው የያዙትን ሥልጣናቸውን ለማቆየት ሲሉ ሁሉቱን የ ኦሮሞና የ አማራ ታላላቅ ማህበረስቦች ለ25 ዓመት የሌለ ታሪክ ፈጥረው እርስ በርስ ለማናቀስ ብዙ ሄደዋል፤ ብዙም አድረገዋል። አሁን ያ ሴራቸው ተንቅቶበት የተንኮል ደባቸው ተደርምሷል። ለዚህም ነው የወያኔው አፈቀላጤ ጌታቸው ረዳ እንዴት ሁለት “ቤንዚንና ውሃ የሆኑ ጠባብና ትምክሕተኞች” አንድ ሆኑ ብሎ ፀጉሩን የነጨው። ከብሽቀቱ የተነሳ እውነታውን ከዶ ላለመቀበል ሲያቃስት ትንፋሽ ያጥረዋል። ይሄንን የህዝብ እዉነታ ለማስተባበል ሃቁን ደብቆ ይህ የሆነው እነርሱ አንድ ስለሆኑ ሳይሆን በእኛ በኩል ብዙ ያልሠረናው ስራ እንዳለ ማሳያ ነው ብሎ ቁጭቱን ገልጿል።

ይሄ ቁጭት ሁሉንም የ ትግሬ ነጻ አዉጭ ነን ባዮችን የገለጠ እዉነታ ነው ። ሁሉንም በዕኩል ትኩሳት ስጋት ላይ የጣለም ጉዳይ ነው፤ ይሁንና ፈረንጆች እንደሚሉት The Game is Over ነውና መደንገጣቸው የሚጠበቅ ነው ። በነገራችን ላይ ተንኮለኝነትና ሴረኝነት እስኪነቃበት ደረስ ነው። አንዴ ከተነቃበት ግን እንደ ሸራብ ክር ይተረተራል።
ሴረኝነት ሁሌም ቢሆን የፈሪዎች መሣሪያ ነው። ለሴራና ለሸር ደግሞ ከትግሬ ነጻ አዉጭ በላይ የት ይገኛል.?

ግደይ ዘርአጽዮን እሱ እስከነበረበት ደረስ የነበረው ወያኔ ለ ትግራይ ህዝብ «መሲህ» እንደነበር አይነት አስመስሎ በድፍረት ሲነግረን ሞክሯል ። አሳዛኝና የሚደንቅ ነው። ግደይ ዘርአጽዮን ዛሬም ደረስ ለተጋሩ ህዝብ ያለውን ንቀት ገላጭ ነው። የትግራይ ህዝብን ፈጅተው እዚህ ለመድረሳቸው ዛሬም ቢሆን አይኑን በጨው አጥቦ ሊክድ ይሞክራል። እንደ እርሱ እና መሰሎች አባባል ሁሉን ነገር ያደረጉት አሁን በሥልጣን ላይ ያሉት ናቸው ብለው ተጨፈኑና እናሞኛችሁ ይሉናል። ግን አሁን ተነቅቶባቸዋል። ጊዜችያችሁ አቀትሟል። አልሰማችሁ ይሆን….? ዛሬ እኮ ያ የድንቁርና እብሪት ተንፍሶ መታውቂያ እስከቀመቀየር እና ትግሬነትን እስከመደበቅ ተደርሷል። የአዲስ አበባን የቀበሌ ቢሮ ደዉላችሁ ማረጋጋጥ ነው። አዲስ አበባ ዛሬ የቀበሌ ቢሮዎች በሙሉ መታውቂያን ለማስቀየር በትግርኛ ተናጋሪዎች ሠልፍ ተጨናንቀው ይገኛሉ። እዩኝ እዩኝ ያሰኘ እብሪት አሁን ደግሞ ደብቁኝ ደብቁኝ እስከማለት ቢያደረሰም፣ ግን አሁን ጊዜው ዘግይቷል።

በእውነቱ ለአቶ ገብረመድህን አርዓያ ረጂም እድሜ ይስጣቸዉና እነ ግደይ ማድረግ ስላለባቸው ነገር መፍትሄውን በተደጋጋሚ ነግረዋቸዋል ። ስለሆነም ለአቶ ግደይ እና መሰሎች በሙሉ፣ መፍትሄውና ከአይምሮ ፀፀታችሁ መውጫ መንገዱ ፣ ላደረግነው ነገር ሁሉ እንፀፀታልን እናም የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ እንጠይቃለን ብሎ ከህሊና ስቃይ መገላገል ነው። በተረፈ ጊዜያችሁ መሽቷል። በጣም የሚያሳዝነውና ህሊናን የሚቆጠቁጠው እናንተ በፈጠራችሁት እና በሠራችሁት ጦስ የትግራይን ህዝብ አጣብቂኝ ውስጥ መከተታችሁ ነው።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!
ኦክቶበር 12 /2016